# የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ

ህዝብ ግንኙነት

# Ethiopian Citizens for Social Justice

Public Relations


**የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)** አባላት እና አመራር በዛሬው እለት በመተከል ዞን በቡልን ወረዳ በቡክጂ ቀበሌ በተጨፈጨፉ ወገኖቻችን የተሰማንን ጥልቅ ሐዘን እንገልፃለን።

የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልልዊ መንግሥት የዜጎች መሰረታዊ መብት የሆነውን በሕይወት የመቆየት መብት ማስከበር ባለመቻሉ እና ድርጊቱ እየተደጋገመ በመምጣቱ ኢዜማ በኢፌደሪ በሕገ መንግሥት አንቀፅ 51/14፣ እና ይሄን ለማስፈጸም በወጣው አዋጅ ቁጥር 359/1995 መሰረት ጉዳዩን በአስቸኳይ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማምጣት እስካሁን የተፈጸሙት አሰቃቂ ወንጀሎችን ማስቆም ያልቻለበትን እውነተኛ መንስዔ የሚያጣራ ኮሚቴ አቋቁሞ በአፋጣኝ ተጠያቂነትን እንዲያሰፍን እና የፌደራል መንግሥት በሕግ አግባብ ጣልቃ በመግባት የዜጎቹን ሕይወት የመጠበቅ እና ሕግ የማስከበር ሥራውን ከማስጠበቅ በተጨማሪ አጥፊዎችን እና በክልሉ ያሉ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ አመራሮችን ተጠያቂ እንዲያደርግ እናሳስባለን።

ታህሳስ 14 2013